# ቅድሚያ ደምን ገድብ!



ተውሀና ተደም የቱ ቢወፍር ነው፣
ምሁር ፕሮፌሰር ጠበብት ተብየው፣
ተአማራ ደም ለዓባይ ቅድሚያ የሚሰጠው?

ተው እግዜርን ፍራ ትዕዛዙን መጣስ ነው፣
በአምሳሉ መጥኖ ግዮን ዳር የሰራው፣
በመላ አገሪቱ የደም ጎርፍ ሲጠርገው፣
በዓባይ መሸፋፈን የሰይጣን ሥራ ነው!

የአማራ ደም በቦይ ታገር ውጪ ሲወጣ፣
ጉራ ፈርዳ ፈሶ ኬንያ ሲገባ፣
ባሌ አሩሲ ጎርፎ ሶማሌን ሲያለማ፣
ሀረር ድሬ ዘንቦ ሸበሌን ሲያቀላ፣
ዓባይ ዓባይ ይላል አለቅላቂ ሁላ!

የአማራ ደም ሲፈስ የሚገጥም ከንፈሩ፣
ዓባይን ሊጠጣ ቦርቀቅ ይላል አፉ፡፡

ለሰላሳ ዓመታት ደሙን ያፈሰሱ፣
ስፍስፍ ብለዋል ውሀውን ሊጠጡ፡፡

የአማራ ደም ሲፈስ እንደ ሬት ሳይመረው፣
ዓባይ ላይ ይንጣጣል ቅቤ ምላሳቸው፡፡

ወለጋ ላይ ፈሶ ሱዳን የሚዘልቀው፣
ተወልቃይት ዘንቦ ገዳሪፍን አልሚው፣
መተከል ላይ ጎርፎ ካርቱም የሚደርሰው፣
ራያ ተደፍቶ ጅቡቲ እሚገባው፣
ወፍራም የአማራ ደም ሳያሳስባቸው፣
የሚፈርሰው ግድብ አንገበገባቸው፡፡

አድር ባይ ሆዳሞች ተአምላክ የተጣሉ፣
የሚፈስ ደም ትተው ውሀ ያቀናሉ፡፡

ግብጥ ሀያሉን አገር ስታንገራግረው፣
ይህ አድግ ታዝዞ ድንጋዩን ቆለለው፣
ተመልሳ ደግሞ ጌታዬ ስትለው፣
ይህ አድግ ታዝዞ ቁልሉን አፍራሽ ነው፣
የሌላው ማረጥረጥ ከንቱ ነው ከንቱ ነው!

ይልቅስ ልብ ግዛ ተማርኩ ባይ መንጋው፣
ለሰላሳ ዓመታት ጎርፎ ያላባራው፣
በአራቱም አቅጣጫ ሲፈስ ግድብ ያጣው፣
የዓባይ ወሀ ሳይሆን የአማራዎች ደም ነው፡፡

ስለዚህ ምሁር ሆይ ስከን ሽምት አደብ፣
ውሀውን ተውና ቅድሚያ ደምን ገድብ፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.

ተያያዥ ጦማሮች

1. *ዘልዛሎች ቀይ ባህርን የሸጡ ባንዳዎች ዓባይን ያድናሉ ብለው የማይጨበጥ ጅራታቸውን አሁንም እየተከተሉ ነው!* *http://ethiopatriots.com/pdf/zelazaloch-key.pdf*

2. *መንጋ ሆይ! እሽ ዓባይስ ያንተ ነው! ዘር ለማጣፋት የታረዱት ዜጎችስ የማን ናቸው?* *http://www.ethiopatriots.com/pdf/Abay-yene-naw.pdf*

3. *The Bond, Fund and Dam Preaching Intellectuals, Why Your Pens Dry to Write about Amara Genocide?* *https://fonkaye.com/2020/07/26/the-bond-fund-and-dam-preaching-intellectuals-why-your-pens-dry-to-write-about-amara-genocide-2/*